www.abyssinialaw.com




| 14ኛ ዓመት ቁጥር 5<br>14th Year No 5 | ባህር ዳር የካቲት 20 ቀን 2001 ዓ.ም<br>Bahir Dar 27th, March 2009 |
|---|---|


# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ዝክረ-ሕግ

# ZIKRE-HIG OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA


| | | | |
|---|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ<br>ብር 21.58<br>Price | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE | የፖ.ሣ.ቁ. 312<br>P.O. Box 312 |


| ማውጫ | CONTENTS |
|---|---|
| ደንብ ቁጥር 65/2001 ዓ.ም<br>በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው የከተሞች አደረጃጀት ፈርጅ መወሰኛና ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ | Regulation No. 65/2009<br>The Amhara National Regional State the Revised Cities' Organizational Category Determination and Establishment, Council of the Regional Government Regulation |

## ደንብ ቁጥር 65/2001 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው የከተሞች አደረጃጀት ፈርጅን ለማቋቋምና ለመወሰን የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ

## REGULATION NO. 65/2009

A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE REVISED CITIES' ORGANIZATIONAL CATEGORY DETERMINATION AND ESTABLISHMENT IN THE AMHARA

www.abyssinialaw.com



NATIONAL REGIONAL STATE

የብሔራዊ ክልሉን ከተሞች ግልጽና ተገቢ የሆኑ መመዘኛዎች አውጥቶ በፈርጆችና በንዑሳን ፈርጆች ማደራጀት ሚናቸውን ከወዲሁ ለይተው ለክልሉ ሁለንተናዊ ልማትና ዕድገት ዕውን መሆን የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት እንደሚያስችላቸው በመታመኑ፣

WHEREAS, it is believed that organizing cities of National Region into categories and sub-categories on the basis of clear and appropriate criteria would enable them to identify their roles in advance and to make their contributions for the realization of all rounded development and progress of the region;

የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ከተሞች ማቋቋሚያ ማደራጃና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 91/1996 የክልሉ ከተሞች ደረጃ መመዘኛና የሚደራጁበት ደንብ እንዲወጣ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር የደነገገ በመሆኑ፣

WHEREAS, Article 4, sub-article 2 of the Revised Amhara National Regional Cities Establishment, Organization and Determination of Powers and Duties Proclamation No. 91/2003 stipulates that a regulation would be issued setting the criteria for grades of cites and their organization thereof;

ከዚህ በፊት ወጥቶ ሥራ ላይ የነበረው ደንብ የከተሞችን ፈጣን የልማት እንቅስቃሴና ተዛማጅ ጉዳዮችን ግምት ውስጥ በማስገባት ከተሞች ከየደረሱበት ደረጃና የመፈፀም አቅም አንፃር ማሻሻል በማስፈለጉ፣

WHEREAS, Having been taken into account rapid development activities and related issues of cities and with regard to grade of cities and their execution capacity, it has been necessary to revise the previous enacting regulation thereof;

የክልሉ ከተሞች በግልጽና በፍትሀዊ መመዘኛዎች እና መስፈርቶች መሠረት እየተመዘኑ ከደረጃ ደረጃ የሚሸጋገሩበትን ሥርዓት መዘርጋት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

WHEREAS, it has been found appropriate to put in place a system through which the regional cities are to be, having been evaluated on the basis of clear and fair measurements and criteria, upgraded from one grade to another thereof;

የብሔራዊ ክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 ድንጋጌ ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

NOW, therefore, the Council of the Amhara Regional Government, in accordance with the powers vested in it under the provisions of article 58, sub. Article 7 of the revised regional constitution, hereby issues this regulation.

www.abyssinialaw.com



# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው የከተሞች አደረጃጀት ፈርጅ መወሰኛና ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 65/2001 ዓ.ም"ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ የተመለከቱት ሁሉ ትርጓሜያቸው በተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ ከተሞች ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ሥልጣንና ተግባራትን መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 91/1996 ዓ.ም የተሰጠው ትርጓሜ በቀጥታ ጥቅም ላይ ይውላል።

## 3. የከተሞች ፈርጅና አደረጃጀት መመዘኛዎች

በብሔራዊ ክልሉ ውስጥ የሚገኙ ከተሞችን ፈርጅና አደረጃጀት ለመወሰን የሚከተሉት መመዘኛዎች በሥራ ላይ ይውላሉ፣

ሀ/ የሕዝብ ብዛት፣

ለ/ የገቢ አቅም፣

ሐ/ የነዋሪዎች መተዳደሪያ /የሥራ መስክ/፣

# PART ONE

# GENERAL

## 1. Short Title

This regulation may be cited as "The Revised Amhara National Regional State Cities' Organizational Category, Determination and Establishment, Council of Regional Government Regulation No. 65/2001."

## 2. Definition

Unless the context requires otherwise, in this regulation all terms and phrases contained in this regulation shall have the meanings accorded to them by the revised Amhara National Regional cities Establishment, organization and Determination of Powers and Duties Proclamation No.91/2003.

## 3. Criteria for the Categories and organization of cities

To determine categories and organization of cities within the National Region, it shall be on the bases of the following criteria:

A. Population size;

B. Potential of revenue;

C. Occupation of city residents;

www.abyssinialaw.com



መ/ እስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ

D. Strategic importance;

## 4. የከተሞች የደረጃ አመዳደብ

በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ከተማ ከሚከተሉት የከተማ ፈርጆች በአንዱ ሊመደብ ይችላል።

1. የከተማ አስተዳደር ከተማ
2. የማዘጋጃ ቤት ከተማ
3. ታዳጊ ከተማ

## 4. Grade Categorization of Cities

Any city within the region may fall into one of the following city categories:

A. City Administration Level City ;

B. Municipal city;

C. Emerging town;

## 5. ከተሞችን በንዑስ ፈርጆች ስለመመደብ

ማንኛውም በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የከተማ አስተዳደር ከተሞችና የማዘጋጃ ቤት ከተሞች በሚከተሉት ንዑስ ፈርጆች ይመደባሉ።

### 1. የከተማ አስተዳደር ከተማ ንዑስ ፈርጆች

በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም የከተማ አስተዳደር አቋም ለማግኘት ብቁ የሆነ ከተማ ከሚከተሉት ንዑስ ፈርጆች በአንደኛው ይደራጃል።

ሀ/ አነስተኛ ከተማ አስተዳደር ከተማ

ለ/ መካከለኛ ከተማ አስተዳደር ከተማ

ሐ/ ሜትሮፖሊታን ከተማ አስተዳደር ከተማ

### 2. የማዘጋጀ ቤት ከተማ ንዑስ ፈርጆች

በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም የማዘጋጃ ቤት ከተማ አቋም ለማግኘት ብቁ የሆነ ከተማ ከሚከተሉት ንዑስ ፈርጆች በአንደኛው ይደራጃል።

## 5. Sub-Categorization of Cities

Any city administration level city and municipal town within the region shall fall into the following sub-categories

### 1. Sub-Categories of City Administration level city

Any city which acquires city administration status within the region shall be organized in one of the following sub-categories:

A. Small city administration level city

B. Medium city administration level city

C. Metropolitan city administration

### 2. Sub-Categories of Municipal City

Any city which acquires municipal city status within the region shall be organized in one of the following sub-categories.

www.abyssinialaw.com



ሀ/ መሪ ማዘጋጃ ቤት ከተማ

ለ/ ንዑስ ማዘጋጃ ቤት ከተማ

A. Lead municipal city

B. Sub-municipal city

## 6. በየደረጃው በፈርጅ የሚደራጁ ከተሞች መነሻ መመዘኛ መስፈርቶች

1.የሜትሮፖሊታን ከተሞች መመዘኛዎች

ሀ/ የሕዝብ ብዛት፡- በከተማው የሚኖረው የሕዝብ ብዛት 150,000 እና በላይ የሆነ

ለ/ የገቢ አቅም፡- በከተማው የሚሰበሰበው አማካይ ዓመታዊ የገቢ መጠን በተለይም ከመሬት ሊዝ ሽያጭ ውጭ ብር 10 ሚሊዮን እና በላይ የሆነ

ሐ/ የነዋሪዎች መተዳደሪያ /የሥራ መስክ/፡- በከተማው ውስጥ ከሚኖረው አጠቃላይ

መ/ እስትራቴጅካዊ ጠቀሜታ፡-

- ለኢንቨስትመንት ምቹ የሆነ
- አመቺ የትራንስፖርት ፍሰት ያለው
- በተመረጡ የልማት ኮሪደሮች ለልማት ማዕከልነት የተመረጠ
- የቱሪዝም ሃብት /ለቱሪዝም አመቺ የሆነ/

በአባሪው የተጠቀሰውን መስፈርት ስሌት ሙሉ በሙሉ /100%/ የሚያሟላ

ሠ/ በአባሪው የተመለከተውን መስፈርት ሙሉ በሙሉ ባያሟላም ከተማው

## 6. Initial criteria for cities to be organized in a category at all level

1. **Criteria for Metropolitan Cities**

A. Population size: where the population of the city is 150,000 and more;

B. Potential of revenue: where the size of average annual income collected in the city, specifically other than land lease sale, is birr 10,000,000 (Ten million birr) and more;

C. Occupation of city residents: where 80% and more, of the total population of the city residents, engage in an occupation other than agriculture;

D. Strategic importance, where it:

- is conducive to investment;
- has conducive transportation flow;
- is selected for development center in selected development corridors;
- is conducive to tourism resource and /or tourism

The city that fully meets the criteria specified in the annexe;

E. Where the regional government specifically decides upon it with regard

www.abyssinialaw.com



ሊሰጠው ከሚችለው ልዩ ጠቀሜታ አኳያ የክልሉ መንግስት በልዩ ሁኔታ ከወሰነ

to special benefits which the city may contributes to, however, provided that how it does not meet the criteria specified in the annexe thereof.

2. **መካከለኛ ከተማ አስተዳደር ከተሞች መመዘኛዎች፡-**

ሀ/ የሕዝብ ብዛት ፡- ከተማው የሚኖረው ሕዝብ ብዛት 50,000 እና በላይ የሆነ፣

ለ/ የገቢ አቅም፡- የገቢ አቅሙ በተለይም ከመሬት ሊዝ ሽያጭ ውጭ 4 ሚሊዮን ብር እና በላይ በአማካይ በዓመት መሠብሠብ የሚችል፣

ሐ/ የነዋሪዎች መተዳደሪያ/ የሥራ መስክ/፡- በከተማው ክልል ውስጥ ከሚኖረው ጠቅላላ ሕዝብ 70% እና በላይ የሆነው ከግብርና ውጭ በሆኑ የሥራ መስኮች የተሠማራ ከሆነ፣

መ/ ሌሎች መስፈርቶች በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ቁጥር መ የተመለከተውን መመዘኛ መስፈርት በማካተት በአባሪው የተጠቀሰውን መስፈርት ስሌት 51.175% እና በላይ አሟልቶ ሲገኝ፣

ሠ/ በአባሪው የተመለከተውን መስፈርት ሙሉ በሙሉ ባያሟላም ከተማው ሊሰጠው ከሚችለው ልዩ ጠቀሜታ አኳያ የክልሉ መንግስት በልዩ ሁኔታ

2. **Criteria for Medium City Administration Level Cities**

A. Population size: where the population of the city residents is 50,000 and more;

B. Potential of revenue; where the amount of average annual income, other than land lease sale, is birr 4,000,000.00 /four million birr/

C. Occupation of city residents: where 70% and more, of the total population of the city residents, engage in an occupation other than agriculture;

D. Other criteria: where it meets the criteria point 51.175% and more specified in the annexe including mode of the criteria specified under sub.Art.1 (D) of Art. 6 this regulation hereof;

E. Where the regional government specifically decides on it with regard to special benefits which the city may contribute to, however, provided that it does not fully meet the criteria specified

www.abyssinialaw.com



ከወሰነ።

in the annexe thereof;

3. አነስተኛ ከተማ አስተዳደር ከተሞች መመዘኛዎች፦

ሀ/ የህዝብ ብዛት፦ በከተማው የሚኖረው የሕዝብ ብዛት 25,000 እና በላይ ከሆነ፣

ለ/ የገቢ አቅም፦ በከተማው የሚሰበሰበው አማካይ ዓመታዊ ገቢ በተለይም ከመሬት ሊዝ ሽያጭ ውጭ 1.5 ሚሊዮን ብር እና በላይ ከሆነ፣

ሐ/ የነዋሪዎች መተዳደሪያ /የሥራ መስክ/፦ በከተማው ውስጥ ከሚኖረው ጠቅላላ ሕዝብ 60% እና በላይ የሆነው ከግብርና ውጭ በሆኑ የሥራ መስኮች የተሠማራ ከሆነ፣

መ/ ሌሎች መስፈርቶች፦ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ቁጥር መመዘኛ መስፈርት በማካተት በአባሪው የተጠቀሰውን መስፈርት ስሌት 34.48% እና በላይ አሟልቶ ሲገኝ፣

ሠ/ በአባሪው የተመለከተውን መስፈርት ሙሉ በሙሉ ባያሟላም ከተማው

3. **Criteria for small city administration level city**

A. Population size: where the population of city residents is 25,000 and more;

B. Potential of revenue: where the amount of average annual income, other than land lease sale, is birr 1,500,000 / one million five hundred thousand birr/ and more;

C. Occupation of city residents: where 60% and more, of the total population of the city residents, engage in an occupation other than agriculture;

D. Other criteria: where it meets the criteria point 34.48% specified in the annexe, including mode of the criteria specified under sub. Article 1(D) of Article 6 of this regulation hereof;

E. Where the regional government specifically decided upon it with regard to special benefits which the city may

www.abyssinialaw.com



ሊሰጠው ከሚችለው ልዩ ጠቀሜታ አኳያ የክልሉ መንግስት በልዩ ሁኔታ ከወሰነ።

4. የመሪ ማዘጋጃ ቤት ከተማ መመዘኛዎች

ሀ/ የህዝብ ብዛት፡- በከተማው ውስጥ የሚኖረው ሕዝብ ቁጥር 10,000 እና በላይ ሆኖ ሲገኝ፣

ለ/ የገቢ አቅም፡- በሊዝ የሚተዳደሩም ሆነ በሊዝ የማይተዳደሩ ከተሞች ከመሬት ሊዝ ሽያጭ ውጭ በዓመት በአማካይ 500 ሽህ ብር እና በላይ ገቢ መሰብሰብ የሚችል የሆነ ከተማ፣

ሐ/ የነዋሪዎች መተዳደሪ /የሥራ መስክ/፡- በከተማው ውስጥ ከሚኖረው ጠቅላላ ህዝብ 50% እና በላይ ከግብርና ውጭ በሆነ የሥራ መስክ የተሠማራ ከሆነ

መ/ እስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ፡-

- በልማት ማዕከልነት ሊያገለግሉ የሚችሉ፣
- የቱሪስት መስህብ ያላቸው /ለቱሪዝም አመች የሆኑ/
- በትራንስፖርት ፍሰታቸው የተሻሉ የሆኑ፣

በአባሪው በተመለከተው መስፈርት ስሌት መሠረት 16.445% እና በላይ የሚያሟሉ፣

ሠ/ ከላይ በተዘረዘሩት መስፈርቶች ስሌት መሠረት አነስተኛውን መመዘኛ ባያሟላም ማንኛውም የወረዳ ከተማ

contribute to, although it does not fully meet the criteria specified in the annexe thereof;

4. **Criteria for Lead Municipal City**

A. Population size: where the population of city residents is 10,000 and more;

B. Potential of revenue: where it may, in both lease system governed and non-lease system governed cities, collect, other than land lease sale, on average birr 500,000 /five hundred thousand birr/;

C. Occupation of city residents: where 50% and more, of the population of city residents, engage in an occupation other than agriculture;

D. Strategic importance:

- Those cities which serve as a development center;
- Those cites having tourist attraction; (conductive to tourism)
- Those cities which are better in their transport flow

Those that meet the point 16.445% and more in accordance with the criteria specified in the annexe thereof;

E. Where it is a center /seat/ of Woreda Administration although it does not meet minimum criterion in accordance

www.abyssinialaw.com



አስተዳደር ማዕከል /መቀመጫ/ የሆነ፣

ረ/ በአባሪው የተመለከተውን መስፈርት ሙሉ በሙሉ ባያሟላም ከተማው ሊሰጠው ከሚችለው ልዩ ጠቀሜታ አኳያ የክልሉ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ በልዩ ሁኔታ ከወሰነ።

5. የንዑስ ማዘጋጃ ቤት ከተማ መመዘኛዎች

ሀ/ የህዝብ ብዛት፡- በከተማው ውስጥ የሚኖረው ሕዝብ ብዛት 5000 እና በላይ ሆኖ ሲገኝ፣

ለ/ የገቢ አቅም፡- ከመሬት ሊዝ ሽያጭ ውጭ በዓመት በአማካይ 50 ሽህ ብር እና በላይ ገቢ መሰብሰብ ይችላል ተብሎ ከተገመተ፣

ሐ/ የነዋሪዎች መተዳደሪ /የሥራ መስክ/፡- በከተማው ውስጥ ከሚኖረው ጠቅላላ ህዝብ 30% እና በላይ ከግብርና ውጭ በሆነ የሥራ መስክ የተሠማራ ከሆነ

መ/ እስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ፡-

በልማት ማዕከልነት ሊያገለግሉ የሚችሉ፣

- የቱሪስት መስህብ ያላቸው /ለቱሪዝም አመች የሆኑ/፣
- በትራንስፖርት ፍሰታቸው የተሻሉ የሆኑ፣

በአባሪው በተመለከተው መስፈርት ስሌት መሠረት 10.355% እና በላይ የሚያሟሉ፣

with mode of the criteria specified hereinabove;

Where the Regional Works and Urban Development Bureau specifically decides upon it with respect to special benefits which the city may render thereof, however, provided that it does not fully meet the criteria specified in the annexe thereof.

5. **Criteria for Sub-Municipal City**

A. Population size: where the population of city residents happened to be 5000 and above;

B. Potential of revenue: where it is estimated that it may be able to collect income, on average, 50,000 birr /fifty thousand birr/ and more

C. Occupation of city residents; where 30%, of the city residents, engage in an occupation other than agriculture;

D. Strategic importance:

⇨ Those which serve as a development center;

⇨ Those having tourist attraction;

⇨ Those which are better in their transport-flow;

Those that meet the point 10.355% and more in accordance with mode of the criteria specified in the annexes thereof;

www.abyssinialaw.com



ሠ/ በአባሪው በተመለከተው መስፈርት ሙሉ በሙሉ ባያሟላም ከተማው ሊሰጠው ከሚችለው ልዩ ጠቀሜታ አኳያ የክልሉ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ በልዩ ሁኔታ ከወሰነ።

6. ታዳጊ ከተማ መመዘኛ መስፈርት

ሀ/ የህዝብ ብዛት፡- በከተማው ውስጥ የሚኖረው ሕዝብ ብዛት 2000 እና በላይ ሆኖ ሲገኝ፣

ለ/ የገቢ አቅም፡- ከመሬት ሊዝ ሽያጭ ውጭ በዓመት በአማካይ 25 ሽህ ብር እና በላይ ገቢ መሰብሰብ ይችላል ተብሎ ከተገመተ፣

ሐ/ የነዋሪዎች መተዳደሪ /የሥራ መስክ/፡- በከተማው ውስጥ ከሚኖረው ጠቅላላ ህዝብ 20% እና በላይ ከግብርና ውጭ በሆነ የሥራ መስክ የተሠማራ ከሆነ

መ/ እስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ፡-

- በልማት ማዕከልነት ሊያገለግሉ የሚችሉ፣
- የቱሪስት መስህብ ያላቸው /ለቱሪዝም አመች የሆኑ/
- በትራንስፖርት ፍሰታቸው የተሻሉ የሆኑ፣

በአባሪው በተመለከተው መስፈርት ስሌት

Where the Regional Works and Urban Development Bureau specifically decides upon it with respect to special benefits which the city may render thereof, however, provided, that it does not fully meet the criteria specified in the annex thereof;

6. **Criteria for Emerging Town**

A. Population size: where the population of city residents is 2000 and more;

B. Potential of revenue: where it is estimated that it may be able to collect income, on average, other than land lease sale, is birr 25,000 /twenty five thousand birr /and more;

C. Occupation city residents: where 20%, of the total population of city residents, engage in an occupation other than agriculture;

D. Strategic Importance

- Those cities which may serve as a development center;
- Those cities having tourist attraction /conductive to tourism/
- Those which are better in their flow of transportation

Those cities that meet point 6.857% and more, in accordance with mode of the

www.abyssinialaw.com



መሠረት 6.857% እና በላይ የሚያሟሉ፣

ሠ/ በአባሪው በተመለከተው መስፈርት ሙሉ በሙሉ ባያሟላም ከተማው ሊሰጠው ከሚችለው ልዩ ጠቀሜታ አኳያ የክልሉ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ በልዩ ሁኔታ ከወሰነ።

## 7. ከተሞችን በየፈርጁ ስለመወሰን

በክልሉ የሚገኙ ከተሞች ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው አባሪ እንደተመለከተው ፈርጃቸው ተወስኗል።

## 8. የከተማ ፈርጆችን ስለማሻሻል

1. የከተማ ፈርጆች አመዳደብ ልዩ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር በየአምስት ዓመቱ ይከለሳል። ክለሳው በሚከናወንበት ጊዜ ደንቡን ማሻሻል ሳያስፈልግ የከተሞችን ደረጃ የማሻሻል ሥራ ብቻ ሊከናወን ይችላል።
2. የከተማ ፍረጃ አመዳደብ ማሻሻያ በቢሮው ተጠንቶና ለክልል መስተዳድር ም/ቤቱ ቀርቦ ውሣኔ ሲያገኝ ይተገበራል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተመለከተው ቢኖርም ከመሪ ማዘጋጃ ቤት ከተማ ጀምሮ ወደታች ላሉ የከተማ ደረጃ እና ፈርጅ የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ሊወሰን ይችላል።

criteria specified in the annex thereof;

Where the Regional Works and Urban Development Bureau specifically decides upon it with respect to special benefits which the city may render thereof, however, provided that it does not fully meet the criteria specified in the annex thereof.

## 7. Categorization of Cities

Cities within the region have been categorized as it is specified in the annex attached to this regulation

## 8. Adjustment of Categorization of Cities

1. Except under special circumstances, the categorization of cities shall be reviewed every five years. While it is being reviewed, only grades of cities may be adjusted without revising the regulation
2. The adjustment of city categorization shall, having been studied by the Bureau and submitted to the council of Regional Government for approval, be implemented thereof.
3. Notwithstanding the provision of sub. Art.2 of this Article hereof, Works and Urban Development Bureau may decide on grade and categorization of cities of lead municipal city and lower town level thereto.

www.abyssinialaw.com



## ክፍል ሁለት
## ስለከተሞች ወሰንና አከላለላቸው

## PART TWO
## BOUNDARIES OF CITIES AND THEIR DELINEATION

### 9. የከተማ አስተዳደር ከተማ ወሰን

1. የአነስተኛ ከተማ አስተዳደር ከተሞች ወሰን ከየከተሞቹ ማዕከላዊ ስፍራ በመነሳት በዙሪያቸው እንደ ሁኔታው 3 ኪሎ ሜትር የአየር ርቀት ራዲየስ ዙሪያ ያለውን መልከዓ-ምድራዊ ክልልና በውስጡ የሚኖሩ ህዝቦችን ያጠቃለለ ይሆናል።
2. የመካከለኛ ከተማ አስተዳደር ከተሞች ወሰን ከየከተሞቹ ማዕከላዊ ስፍራ በመነሳት በዙሪያቸው እንደሆኔታው 5 ኪሎ ሜትር የአየር ርቀት ራዲየስ ዙሪያ ያለውን መልከዓ-ምድራዊ ክልልና በውስጡ የሚኖሩ ህዝቦችን ያጠቃለለ ይሆናል።
3. የሜትሮፖሊታን ከተማ አስተዳደር

### 9. Boundaries of City Administration Level City

1. The boundaries of small city administration level city shall, depending on circumstances, encompass all land within a radius of 3 kilometers form the center of the city and all people living therein
2. The boundaries of middle city administration level city shall, depending on circumstances, encompass all land within a radius of 5 kilometers form the center of the city and all people living therein
3. Starting form the center of the city, the

www.abyssinialaw.com



ከተማ ወሰን ከማዕከላዊ የከተማው በመነሳት፡-

ሀ/ በዙሪያው 10 ኪሎ ሜትር የአየር ራዲየስ የሚገኘውን መልከአ-ምድራዊ ክልልና በውስጡ የሚገኘውን ኗሪ ሕዝብ፣

ለ/ በአማካይ 20 ኪሎ ሜትር ራዲየስ የሚገኙ የተወሰነና የአካባቢ አስተዳደር አቋም ያላቸው ከተሞችንና በውስጣቸው የሚገኘውን ኗሪ ሕዝብ ያጠቃልላል።

## 10. የማዘጋጃ ቤት ከተሞች ወሰን

የመሪና የንዑስ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች ወሰን ከየከተሞቹ ማዕከላዊ ቦታ በመነሳት በዙሪያቸው እንደ ከተማው ዕድገት ደረጃ ከ1 እስከ 2 ኪሎ ሜትር ራዲየስ ያለውን መልከዓ-ምድራዊ ክልልና በውስጡ የሚኖሩ ሕዝቦችን ያጠቃለለ ይሆናል።

## 11. የታዳጊ ከተሞች ወሰን

የታዳጊ ከተሞች ወሰን ከከተማው ማዕከላዊ ቦታ በመነሳት በዙሪያው እንደከተማው ዕድገት ሁኔታ ከ0.5 ኪ.ሜትር እስከ 1 ኪሎ ሜትር ራዲየስ ያለውን መልከዓ-ምድራዊ ክልልና በውስጡ የሚኖሩ ህዝቦችን ያጠቃለለ ይሆናል።

## 12. ስለከተሞች ወሰን አካላይ ኮሚቴ

1. አግባብነት ባላቸው የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት የከተማ አስተዳደር ከተሞች ወሰን የሚከልል ኮሚቴ በዞን

boundaries of Metropolitan Administration city shall encompass:

A. The surrounding geographic region lying within radius of 10 kilometers and the population living therein.

B. Cities with a defined local administration status found within an average radius of 20 kilometers and the population living therein

## 10. Boundaries of Municipal Cities

The boundaries of Lead and Sub-municipal cities shall, depending on development level of each city, include the surrounding geographic region within a radius of 1to 2 kilometers from the center of the city and population living therein.

## 11. Boundaries of Emerging Towns

The boundaries of emerging towns shall, depending on the development of each town, include the surrounding geographic region within a radius of 0.5 to 1 kilometers and the population living therein.

## 12. City Boundary Delineating Committee

1. In accordance with the relevant provisions of this regulation, a committee to delineate the boundaries of City Administration

www.abyssinialaw.com



አስተዳደር ጽ/ቤት ይሰየማል።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የማዘጋጃ ቤትና የታዳጊ ከተሞች ወሰን አካላይ ኮሚቴ የሚሰየመው በሚመለከተው ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት ይሆናል።

level cities shall be designated by the zone administrative office

2. Without prejudice to the provision of sub. article 1 of this article hereof, a committee to delineate the boundaries of municipal and emerging towns shall be designated by respective woreda administrative office.

## 13. ስለ ኮሚቴው አሠራርና ኃላፊነት

1. የከተሞች ወሰን አካላይ ኮሚቴ ወሰን ለመከለል የሚጠቀምበትን ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ የክልሉ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ይህን ደንብ መሠረት አድርጐ ያወጣል።

## 13. Working Procedures and Responsibilities of the Committee

1. The Regional Bureau of Works and Urban Development shall, pursuant to this regulation, issue detailed implementation directives that the Boundary Delineating Committee uses to delineate the boundaries of cities.

## 14. ዝርዝር ወሰኑን ስለማፅደቅ፣

1. የወሰን አካላይ ኮሚቴው ለከተማ አስተዳደር የሠራውን ዝርዝር ወሰን በቅድሚያ በክልሉ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ አስተችቶ አስገምግሞ በዞን አስተዳደር ካቢኔ አቅርቦ ያፀድቃል።

2. የወሰን አካላይ ኮሚቴው ለማዘጋጃ ቤትና ታዳጊ ከተሞች የሥራውን ዝርዝር ወሰን በዞን ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ

## 14. Approval of Detailed Boundary Lines

1. The Boundary Delineating Committee shall, having detailed boundary it delineated for city administration level reviewed and evaluated by the Regional Bureau of Works and Urban Development, cause same to be approved by zone administration cabinet.

2. Detailed boundary delineated for municipal and emerging towns by the Boundary Delineating Committee shall,

www.abyssinialaw.com


ታይቶና ተገምግሞ በወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ይፀድቃል።

## 15. የከተማ ወሰንን ስለማሻሻል

የአንድ ከተማ ወሰን በደረጃ ለውጥና ሽግግር ምክንያት ከላይ በተዘረዘሩት አግባቦች ከተከለለ በኋላ እንደከተማው የዕድገት ሁኔታ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች ማሻሻል ሲያስፈልግ፣

1. ጉዳዩ የከተማ አስተዳደር ከተሞችን የሚመለከት ከሆነ የሚመለከተው ከተማ አስተዳደር ጥያቄውን ለክልሉ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ሲያቀርብ በክልሉ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ በኩል ከታዬ በኋላ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ቀርቦ ይወሰናል።

2. ጉዳዩ የሚመለከተው የማዘጋጃ ቤቶችንና የታዳጊ ከተሞችን ከሆነ የወረዳው አስተዳደርና የዞኑ ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ ሲያምኑበት ለወረዳው መስተዳድር ምክር ቤት ቀርቦ ይወሰናል።

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

having been reviewed and evaluated by Zone Works and Urban Development Department, be approved by the Council of Woreda Administration.

## 15. Adjustment of City Boundaries

Where, after the boundaries of a city have been delineated in the manner specified above due to grade change and its upgrading and an adjustment becomes necessary depending on the progress of the city or in various reasons:

1. If the matter concerns city administration, the application is presented to the Regional Bureau of Works and Urban Development by the concerned city administration level city and viewed by the Bureau, it shall be presented to and determined by the council of the Regional Government.

2. If the matter concerns municipals and emerging towns, it shall, where the woreda administration and zone Works and Urban Development Department believes in it, be presented to and approved by the woreda Administrative Council.

## PART THREE

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

www.abyssinialaw.com



## 16. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ይህን ደንብ ለማስፈፀም የሚረዱ መመሪያዎችን የክልሉ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ሊያወጣ ይችላል።

## 17. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጐች

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የከተሞች አደረጃጀት ፈርጅ መወሰኛና ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ም/ቤት ደንብ ቁጥር 17/1996 ዓ.ም በዚህ ደንብ ተሽሯል።

2. ይህን ደንብ የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ህግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ ደንብ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

## 18. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር

የካቲት 20 ቀን 2001 ዓ.ም

አያሌው ጐበዜ

የአማራ ብሔራዊ ክልል ርዕሰ መስተዳድር

## 16. Power to Issue Directives

The Regional Bureau of Works and Urban Development may issue directives necessary for the implementation of this regulation.

## 17. Inapplicable Laws

1. The Amhara National Regional State Cities' Organizational Category Determination and Establishments, Council of Regional Government Regulation No.17/2003 shall be repealed by this regulation.

2. Any other regulation, directive or customary practice inconsistent with this regulation shall not apply to matters provided for in this regulation

## 18. Effective Date

This regulation shall come into force as of the day of its deliberation upon and approved by the Council of the Regional Government.

Done at BahirDar

This 27th day of March, 2009

Ayalew Gobezie

Head of Government of the Amhara National Regional State